በየካ ክክፍለ ከተማ ወረዳ **08** ብሩህ ተስፋ ጉድኝት ማዕከል የወጣቶች ገነት ቅ/አ/አ/ደ/ት/ቤት ሳይንስ ት/ት ሞዴል ፈተና ***2016*** ዓ.ም

የጥያቄ ብዛት፦ 40

የተሰጠው ጊዜ፦ 1 ሰ

ስም ---------- ክፍል ------ ቁጥር ---

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በተሰጠው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁሩ

--1. ከሚከተሉት ውስጥ ታዳሽ የሆነው የጉልበት ምንጭ የቱ ነው?


ሀ. ንፋስ ለ. ቤንዚን ሐ. ነጭ ጋዝ መ. ናፍጣ

--2. ግራ አቀባይ ልበገንዳ ከግራ ተቀባይ ልበገንዳ የተቀበለውን ደም በ -------ውስጥ ወደ ተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ይረጫል

ሀ. አኦርታ ለ. ፑልሞናሪ ቬይን

ሐ. ፑልሞናሪ አርተሪ መ. ትልቁ ደም መልስ

ከተራ ቁጥር **3-5** ያለውን ጥያቄ ከታች ያለውን ምስል በመመልከት መልሱ



--3 20^0 ደቡብ ኬክሮስ እና 20^0 ምዕራብ ኬንትሮስን የሚያሳየው ፊደል የቱ ነው?

ሀ. "ለ" ለ. "ሀ" ሐ. "ሐ" መ. "መ"

--4. ፊደል"ሀ" የሚያመለክተው ቦታ ፍፁማዊ መገኛ በዲግሪ ከተቀመጠው ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 10^0 ደቡብ ኬንትሮስ እና 10^0 ምስራቅ ኬክሮስ

ለ. 10^0 ሰሜን ኬንትሮስ እና 10^0 ምዕራብ ኬክሮስ

ሐ. 10^0 ደቡብ ኬክሮስ እና 10^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

መ. 10^0 ሰሜን ኬክሮስ እና 10^0 ምዕራብ ኬንትሮስ

--5. ፊደል"መ" የሚያመለክተው ቦታ ፍፁማዊ መገኛ በዲግሪ ከተቀመጠው ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 10^0 ደቡብ ኬንትሮስ እና 10^0 ምዕራብ ኬክሮስ

ለ. 10^0 ሰሜን ኬንትሮስ እና 10^0 ምስራቅ ኬክሮስ

ሐ. 10^0 ደቡብ ኬክሮስ እና 10^0 ምዕራብ ኬንትሮስ

መ. 10^0 ሰሜን ኬክሮስ እና 10^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

--6. ለኦክስጂንና ለካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ወደ ደም ውሰጥ መግቢያ እና መውጫ ሆኖ የሚያገለግለው የመተንፈሻ አካል ---------- ይባላል።

ሀ. ደቂቅ ትንቧ ለ. ትንከረት ሐ. ባላትንቧ መ. ሰርን

--7. ከሚከተሉት ውስጥ አንድን ነገር ለሁለት ለመክፈል የሚረዳ የቀላል ማሽን አይነት የሆነው የቱ ነው

ሀ. ዘንባይ ወለል ለ. ሽክርክሪትና ዘንግ ሐ. ሽብልቅ መ. መፈንቅል

--8. የዘይትና የውሃ ድብልቅ በየትኛው የመለያ ዘዴ እለያለን

ሀ. ጥሊያ ለ. ቀረራ ሐ. ትነት መ. ንጥረት

--9. ምስራቅ አፍሪካን የሚያዋስኑ የአፍሪካ ሀገራት ስንት ናቸው

ሀ. አምስት ለ. ስምንት ሐ. ሰባት መ. ስድስት

--10. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የገናሌ ወንዝ የሚገኘው በኢትዩጵያ ነው

ለ. የሩቩማ ወንዝ የሚገኘው በታንዛንያና ሞዛምቢክ ድንበር ነው

ሐ. የዛምቤዚ ወንዝ የሚገኘው በኢትዩጵያ ነው።

መ. የአባይ ወንዝ የሚገኘው በኢትዩጵያ ነው

--11. ቀኝ ተቀባይ ልበገንዳ በኦክስጅን ያልበለፀገ ደም ከ -------- ተቀብሎ ወደ ቀኝ አቀባይ ልበገንዳ ይልካል

ሀ. ትልቁ ደም መልስ ለ. ትልቁ ደም ቅዳ

ሐ. አ ኦርታ መ. ሳንባ

--12. ግራ ተቀባይ ልበገንዳ ከሳንባ በኦክስጅን የበለፀገ ደም በ --------- ተቀብሎ ወደግራ አቀባይ ልበገንዳ ይልካል

ሀ. ፑልምናሪ አርተሪ ለ. ፑልሞናሪ ቬይን

ሐ. ሳንባ መ. አኦርታ

--13. እንቁላል ከ እንቁልጢ የመውጣት ሒደት ------- ይባላል

ሀ. እንቁልጢ ለ. ኮረዳነት ሐ. ጉርምስና መ. ውፃት

--14 የፕሌትሌቶች ተግባር የሆነው የቱነው;

ሀ. ከበሽታ መከላከል ሐ. ደም እንዲረጋማድረግ

ለ. ጀርሞችን መከላከል መ. ኦክስጅን ማሰራጨት

-------15. ሜሩ ተራራ የሚገኘው ------- በምትባል ሀገር ነው

ሀ. ኢትዮጵያ ለ. ታንዛንያ ሐ. ኮንጎ መ. ዮጋንዳ

--16. ድንቅነሽ የምትባለው ቅሪተ አካል የተገኘችው --------- በሚባል ቦታ ነው

ሀ. ኮቢፎራ ለ. ሐዳር ሐ. አራሚስ መ. ሔርቶ

--17. በመሬት በዙሪያ የሚሽከረከሩ ሰው ሰራሽ ሳትላይቶችን በመጠቀም የተለያዩ መረጃዎችን ወደ መሬት የሚያቀብሉ መተግበሪያዎች ---------- ይባላሉ።

ሀ. ጂፒኤስ ለ. ጎግል ã ርዝ ሐ. ጎግል ካርታ መ. ጎግል

--18. ዋህድ ዘር ድብልቅ የሆነው የቱ ነው

ሀ. ወተት ለ. የበቆሎና የስንዴ ድብልቅ ሐ. ደም መ. አየር

--19. ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየትና ለመመርመር ስለተለያዩ በሽታዎች ለመከሰት ትንቢያ ለመስጠት የምንጠቀምበት መተግበሪያ የትኛው ነው?

ሀ. ጎግል ማፕ ለ. ጎግል ካርታ ሐ. ጎግል ã ርዝ መ. ጂፒኤስ

--20. ልዩ ዘር ድብልቅ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አየር ለ. ደም ሐ. የጨው ሙሙት መ. የስኳር ሙሙት

--21. በኢምጋት ጊዜ የካርቦንዳይ ኦክሳይድ መጠን ስንት ነው?

ሀ. 16% ለ. 0.3% ሐ. 4% መ. 78%

--22. ከሚከተሉት የመተንፈሻ አካላት መካከል አየርን የሚያሞቅ እንዲሁም ቆሻሻንና ጀርምን የሚያጣራው የቱ ነው?

ሀ. ደቂቅ ትንቧ ለ. ሰርን

ሐ. ትንከረት መ. ዐብይ ትንቧ

--23. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ፈሳሾችን በድብልቅ ውስጥ ባላቸው የነጥበ ፍሌት ልዩነት የምንለይበት ዘዴ ምን ይባላል?

ሀ. ትነት ለ. ንጥረት ሐ. ቀረራ መ. ጥሊያ

--24. ከሚከተሉት ውስጥ ታዳሽ ያልሆነው የጉልበት ምንጭ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ንፋስ ለ. የፀሐይ ብርሃን ሐ. ውሃ መ. የድንጋይ ከሰል

--25. የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በአፍሪካ ውስጥ ብቻ -------- ኪሎ ሜትር ይሸፍናል

ሀ. 5600 ለ. 7200 ሐ. 7000 መ. 6500

--26. ከሚከተሉት ወስጥ ከህንድ ውቅያኖስ ደሴቶች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?

ሀ. ሲሸልስ ለ. ሞሪሽየስ ሐ. ሪዩንየን መ. ሶማሊያ

--27. የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ናሚቢያ ለ. ኤርትራ ሐ. ኢትዮጵያ መ. ኬንያ

--28. የአንታርክቲክ ክበብ የሚገኘው በ---------- ንፍቀ ክበብ ነው

ሀ. ሰሜናዊ ለ. ደቡባዊ ሐ. ምዕራባዊ መ. ምስራቃዊ

--29. በኢትዮጵያ ውስጥ የማይገኘው ሀይቅ የቱ ነው?

ሀ. ላንጋኖ ለ. ዝዋይ ሐ. ቆቃ መ. ቱርካና

--30. ለሰውነታችን ህዋሳት በጣም ቅርብ የሆኑት የደም ስሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ደም መልስ ለ. ደም ቅዳ

ሐ. ቀጣጭን የደም ስሮች መ. አኦርታ

--31. ኦክስጂንና አልሚ ምግቦችን ለሰውነታችን ህዋሶች የሚሰራጭበት እንዲሁም ካርቦንዳይኦክሳይድ እና ሌሎች ቆሻሻዎች በደም አማካኝነት የሚሄድበት ሂደት ምን ይባላል?

ሀ. ትንፈሳ ለ. ደም ኡደት ሐ. ደም መ. የምግብ መፈጨት

--32. በኮረዳነት ወቅት በሴቶች ላይ የማይታየው ስነ ህይወታዊ ለውጥ የትኛው ነው?

ሀ. የድምፅ መቅጠን ለ. የጡት ማጎጥጎጥ

ሐ. የዳሌ መስፋት መ. የድምፅ መጎርነን

--33. የስርአተ ትንፈሳ ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ለማውራት ለ. ለማሽተት

ሐ. በሰውነታችን ውስጥ የሙቀትና ቅዝቃዜን ለማመጣጠን

መ. ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ለህብረ ህዋሶቻችን ማሰራጨት

--34. የኢትዮጵያን ፍፁማዊ መገኛ በትክክል የሚገልፀው የቱ ነው

ሀ. 3^0 ሰሜን - 15^0 ሰሜን ኬክሮስ እና 33^0 ምስራቅ - 48^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ. 3^0 ሰሜን - 15^0 ሰሜን ኬንትሮስ እና 33^0 ምስራቅ - 48^0 ምስራቅ ኬክሮስ

ሐ. 3^0 ሰሜን - 15^0 ደቡብ ኬክሮስ እና 33^0 ምዕራብ - 48^0 ምዕራብ ኬንትሮስ

መ. 3^0 ሰሜን - 15^0 ደቡብ ኬንትሮስ እና 33^0 ምዕራብ - 48^0 ምዕራብ ኬክሮስ

--35. የኪሊማንጃሮ ተራራ የከፍታ መጠን ስንት ነው

ሀ. 5985 ሜትር ለ. 5.110 ሜትር

ሐ. 5200 ሜትር መ. 5895 ሜትር

--36. በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኘው የምስራቅ አፍሪካ ሐይቅ የቱ ነው

ሀ. ጣና ለ. ዝቋላ ሐ. ኪቩ መ. ቪክቶሪያ

--37. የምስራቅ አፍሪካ በስተሰሜን በኩል የሚያዋስነው ውሃማ አካል

የቱ ነው

ሀ. የሰሜን አፍሪካ ሀገራት ሐ. ቀይባህር

ለ. የህንድ ውቅያኖስ መ. የኤደን ባህረ ሰላጤ

--38. የአግድም መስመሮች አጠቃላይ ብዛት ስንት ነው

ሀ. 180 ለ. 360 ሐ. 90 መ. 60

--39. አግድምና ቋሚ መስመሮችን በመጠቀም የአንድን አካባቢ ወይም ሀገር መገኛ የዲግሪ ልኬትን በመጠቀም የምንገልፀው የመገኛ አይነት ---------- ይባላል።

ሀ. አንፃራዊ መገኛ ለ. ፍፁማዊ መገኛ

ሐ. ግምታዊ መገኛ መ. አካባቢያዊ መገኛ

--40. የአርክቲክ ክበብ የሚገኘው በስንት ዲግሪ ላይ ነው

ሀ. 23 $1/2^0$ ሰሜን ለ. 23 $1/2^0$ ደቡብ

ሐ. 66 $1/2^0$ ሰሜን መ. 66 $1/2^0$ ደቡብ

አዘጋጅ ፦ ወጣቶች ገነት ት/ቤት

የወጣቶች ገነት የመ/ያ/ት/ቤት የ **6** ኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ት/ት ሞዴል ፈተና **2016** ዓ.ም

ስም ---------- ክፍል ------ ቁጥር ---

መልስ መስጫ

ምርጫ

1. ሀ	**21.** ሐ
2. ሀ	**22.** ለ
3. ሀ	**23.** ለ
4. መ	**24.** መ
5. መ	**25.** ሀ
6. ለ	**26.** መ
7. ሐ	**27.** ሀ
8. ለ	**28.** ለ
9. ለ	**29.** መ
10. ሐ	**30.** ሐ
11. ሀ	**31.** ለ

12. ለ
13. መ
14. ሐ
15. ለ
16. ለ
17. ሀ
18. መ
19. ሐ
20. ለ
32. መ
33. መ
34. ሀ
35. መ
36. ሐ
37. ሐ
38. ሀ
39. ለ
40. ሐ